-2|2003

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የከተማ ልማትና የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF URBAN DEVELOPMENT AND CONSTRUCTION

ቁጥር
Ref.No. H1-81000250/33

ቀን
Date. 08/07/2003

አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ
ADDIS ABABA - ETHIOPIA

698/3013

**ለሕግ መምሪያ**
**ከ/ል/ኮ/ሚ**

ጉዳዩ፡- **የፀደቀ መመሪያ ስለመላክ**፤

በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም እና ሌሎች የመንግስት ፕሮጀክቶች ለተመረጡ የሥራ ተቋራጮች የተሻሻለ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለመስጠት የወጣ መመሪያ ቁጥር 2/2003 የፀደቀውን ሰነድ ከታህሳስ 27 ቀን 2003 ዓ.ም. ጀምሮ ተግባራዊ እንዲሆን አባሪ በማድረግ ልከናል፡፡

ከሰላምታ ጋር

መኩሪያ ኃይሌ
ሚኒስትር

**ግልባጭ**፤

- ለክቡር ሚኒስትር ጽ/ቤት
- ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ /ኮንስትራክሽን ዘርፍ/
- ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ /ከተማ ልማት ዘርፍ/

**ከ/ል/ኮ/ሚ**

ስልክ/ Tel. 011-553-16-88 011-553-16-72 011-553-16-73
የፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box 24134/1000
ፋክስ /Fax 011-554-12-68
ድህረ ገጽ / Web Site WWW.mudc.Gov.et
E-Mail: mwud_sm@ethionet.et

# የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር

## በተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም እና ሌሎች የመንግስት ፕሮጀክቶች ለተመረጡ አማካሪ አሀዶች የተሻሻለ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ለመስጠት የወጣ መመሪያ

## መመሪያ ቁጥር 698/2013

ታህሣሥ 2003 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

# ማውጫ


መግለጫ....1

መመሪያ ቁጥር 2/2003....2

ክፍል አንድ....3

ጠቅላላ....3

1. አጭር ርዕስ....3

2. ትርጓሜ....3

ክፍል ሁለት....4

ስለምዝገባ....4

3. የምስክር ወረቀት ለማግኘት ሊሟሉ የሚገቡ መሥፈርቶች....4

4. የአማካሪዎች ደረጃ....5

5. ለአማካሪዎች የምዝገባ ጥሪ ስለማድረግ....5

6. ብቁ ያልሆኑ አማካሪ አሃዶች....6

7. የአማካሪ አሀድነት የምሥክር ወረቀት አሰጣጥ....6

8. የአሀዱ ህጋዊ ሰውነት....6

9. የአማካሪ አሀዶች የፕሮጀክት መጠን....7

10. የምሥክር ወረቀትን ስለመሠረዝ....7

11. የምስክር ወረቀትን ስለማገድ....7

ክፍል ሶስት....8

የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት....8

12. አቤቱታ ስለማቅረብ....8

13. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ....9

14. የኮሚቴው የሥልጣን ወሰንና የውሳኔ አሰጣጥ....9

15. ወቅታዊ መረጃ ስለመስጠት....10

16. ጥብቅ ክልከላ....10

ክፍል አራት....11

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች....11

17. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ....11

18. የማስፈፀም ኃላፊነት....11

19. መመሪያውን ስለማሻሻል....11

20. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ....11

## በተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም እና ሌሎች መሰል የመንግስት ፕሮጀክቶች ለተመረጡ አማካሪ አሀዶች የተሻሻለ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ለመስጠት የወጣው መመሪያ

### መግለጫ

የተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም እና መሰል አገር አቀፍ ሽፋን ያላቸው የመንግሥት ፕሮጀክቶች የአማካሪ ድርጅቶች እጥረት እንዳይገጥማቸው ለማድረግ ባለሙያዎችን መርጦ ለአማካሪነት ለማብቃት በተዘጋጀው ፕሮግራም መሠረት መመሪያ በማዘጋጀት፣ ባለሙያዎችን በመመዝገብ፣ በመምረጥ፣ በማሰልጠን እና ትስስር በመፍጠር ቁጥራቸው ከ40 በላይ የሚሆኑ አማካሪ አሃዶች ወደ ሥራ መግባታቸው እና የሚያበረታታ አፈፃፀም የተመዘገበ መሆኑ ይታወቃል።

የተጠቀሰው ቁጥር ያላቸው አማካሪ አሃዶች የተመረጡት በአገር አቀፍ ደረጃ በተጀመሩት እና በመከናወን ላይ በሚገኙት፣

- ለተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም፣
- ለጤና ጣቢያዎች ግንባታ፣
- ለቴሌኮም የሞባይል ማስፋፊያ ፕሮጀክቶች፣
- ለሬዲዮ ማስፋፊያ ፕሮጀክት
- ለተንዳሆ ስኳር የቤቶች ልማት ፕሮጀክት

እንዲሳተፉ ታስቦ የነበረ ሲሆን፣ በአሁኑ ጊዜ ሊገነቡ የታቀዱት ጤና ጣቢያዎች አብዛኛዎቹ አማካሪዎች የተመደቡላቸው በመሆኑ፣ የሞባይል ማስፋፊያ ፕሮጀክቶችም ከአንድ የግንባታ ዙር በኋላ የሚጠናቀቁ በመሆኑ እና በቤቶች ልማት ፕሮጀክት የሚሸፈኑ ከተሞች ቁጥር የሚጨምር ባለመሆኑ የተመረጡትን አማካሪ ድርጅቶች ከተጠቀሱት ፕሮጀክቶች ጋር ብቻ በማስተሳሰር መቀበል አስፈላጊ የማይሆንበት ደረጃ ተደርሷል። ከዚህም የተነሳ አማካሪ አሃዶች በሌሎች ቦታዎችም ተወዳድረው መሥራት የሚችሉባቸውን ሁኔታዎች ማመቻቸት አስፈልጓል።

በዚህም መሠረት ለተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም እና ሌሎች መሰል የመንግሥት ፕሮጀክቶች ባለሙያዎችን መርጦ ለአማካሪነት ለማብቃት በተዘጋጀው መመሪያ መሠረት የተመረጡት እና ወደ ሥራ የገቡት አሃዶች በሚገኙበትም ደረጃቸው በሚፈቀድላቸው ፕሮጀክቶች ላይ መሳተፍ እንዲችሉ ለማድረግ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 691/2003 አንቀፅ 25 /1/ቸ/ ሥር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "ለተመረጡ አማካሪ አሀዶች የተሻሻለ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ለመስጠት የወጣ መመሪያ 698/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

1/ "አማካሪነት" ማለት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 3 ሥር የተመለከቱትን ተፈላጊ መሥፈርቶች የሚያሟሉ ባለሞያዎች በአሀድነት ተደራጅተው የሚሰጡት የማማከር ተግባር ነው።

2/ "የባለሙያዎች የማብቂያ መመሪያ" ማለት ለተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም እና ሌሎች መሰል የመንግሥት ፕሮጀክቶች ባለሙያዎችን መርጦ ለአማካሪነት ለማብቃት በሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የወጣው የ2000 ዓ.ም መመሪያ ነው፤

3/ "አማካሪ አሃድ ወይም አሃድ" ማለት ለተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም እና ሌሎች መሰል የመንግሥት ፕሮጀክቶች ባለሙያዎችን መርጦ ለአማካሪነት ለማብቃት በተዘጋጀው መመሪያ መሠረት ተመርጠው ሥልጠና በወሰዱ ባለሙያዎች የተቋቋመ አማካሪ ድርጅት ማለት ነው፤

4/ "አጠቃላይ መመሪያ" ማለት ከባለሙያዎች ማብቂያ መመሪያ ውጪ ለማስተናገዱ በሥራ ላይ ያለው የምዝገባ መመሪያ ማለት ነው፤

5/ "መመሪያ" ማለት ይህ ለተመረጡ አማካሪ አሀዶች የተሻሻለ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ለመስጠት የወጣ መመሪያ ቁጥር 2/2003 ነው፤

6/ "የአማካሪ ደረጃ " ማለት በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ለአማካሪ ድርጅቶች የሚሰጥ ደረጃ ነው፤

7/ "የምሥክር ወረቀት " ማለት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 3 ሥር የተቀመጡትን መሥፈርቶች ማሟላቱ በሚኒስቴሩ ተረጋግጦ ለአማካሪ አሀዱ የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫ ምሥክር ወረቀት ማለት ነው፤

8/ "ያልተገደበ የምስክር ወረቀት" ማለት አማካሪ አሀዶች በባለሙያዎች የማብቂያ መመሪያ በተፈቀዱላቸው ፕሮጀክቶች ሳይወሰኑ ደረጃቸው በሚፈቅድላቸው ሌሎች ፕሮጀክቶች ሁሉ ለመሳተፍ እንዲችሉ የሚሰጥ የአማካሪነት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማለት ነው፡፡

9/ "መዝጋቢ አካል" ማለት በዚህ መመሪያ መሠረት የሚመዘገቡ አማካሪ አሀዶችን ማመልከቻዎች በመቀበልና በመመርመር የብቃት ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀት እንዲሰጣቸው ወይም እንዳይሰጣቸው እንዲሁም የዲሲፕሊን ጉድለት ሲከሰት የምሥክር ወረቀቱን በራሱ ሥልጣን ለመሠረዝ ወይም የመሠረዙ ሥልጣን የፌዴራል የግዥ እና ንብረት ስተዳደር ኤጀንሲ ሆኖ ሲያገኘው ለዚሁ አካል የማስተላለፍ ኃላፊነት የተሰጠው የሚኒስቴሩ ቢሮ ነው፤

10/ "የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ወይም ኮሚቴው" ማለት መዝጋቢው አካል የምሥክር ወረቀት በመስጠት ሂደት፤ ወይም በዲሲፕሊንና ሌሎች ምክንያቶች መዝጋቢው አካል በሚሰጠው ውሳኔ ላይ የሚቀርበውን ቅሬታ ተቀብሎ የሚያስተናግድ አካል ነው፤

11/ "ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፡፡

## ክፍል ሁለት
## ስለምዝገባ

### 3. የምስክር ወረቀት ለማግኘት ሊሟሉ የሚገቡ መሥፈርቶች

1/ በዚህ መመሪያ ተጠቃሚ የሚሆኑት በባለሙያዎች የማብቂያ መመሪያ መሠረት የተመረጡ እና አማካሪ አሀድ መሥርተው ወደ ሥራ የገቡት ባለሙያዎች ሲሆኑ በማንኛውም ደረጃቸው በሚፈቅድላቸው ፕሮጀክቶች ላይ መሳተፍ የሚያስችላቸው ያልተገደበ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርባቸዋል፡፡

ሀ) የሥራ ትሥሥር በማድረግ በባለቤትነት ፕሮጀክቶቹን ሲያካሄዱ ከቆዩባቸው አሠሪ መሥሪያ ቤቶች ወይንም የፕሮጀክት ጽ/ቤቶች መልካም የሥራ አፈፃፀም የነበራቸው ስለመሆኑ፣

ለ) ከአሠሪ መሥሪያ ቤቶቻቸው ብድር አለመውሰዳቸውን፣ ወይም ብድር ወስደው በብድር ስምምነቱ መሠረት እየከፈሉ ስለመሆኑ ፣

ሐ) በባለሞያዎች የማብቂያ መመሪያ የተመለከቱትን የባለሞያዎች፣ የቢሮ እና የቢሮ መገልገያዎች ስለማሟላታቸው፣

መ) ታክስና ከታክስ ጋር የተገናኙ ግዴታዎችን ስለመወጣታቸው፣ ማስረጃ የሚያቀርቡ መሆን ይኖርባቸዋል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር /1/ሐ/መሠረት ለሚጠየቀው የባለሞያ ስብጥር ነባር ባለሞያ የጎደሉባቸው አባላት ካሁን ቀደም በባለሞያ ማብቂያ መመሪያው መሠረት ተመርጠው ሥልጠና የወሰዱ ባለሞያዎችን በማሟላት መቅረብና መመዝገብ ይችላሉ።

3/ የሥራ ማስኬጃ ወጪን ለመቀነስ፣ ወይም ስብጥራቸው ከተፈቀደው በታች ለሆኑባቸው አህዶች በባለሞያዎች ማብቂያ መመሪያው ከአንድ በላይ ለሆኑ አህዶች እንዲያገለግሉ የተፈቀዱ ባለሞያዎችን በማሟያነት በመጠቀም መቅረብና መመዝገብ ይቻላል።

## 4. የአማካሪዎች ደረጃ

ለአማካሪ አህዶች የሚሰጠው ደረጃ የአማካሪ መሐንዲሶችና አርክቴክቶች (Consulting Engineers and Architects) ደረጃ IV ይሆናል።

## 5. ለአማካሪዎች የምዝገባ ጥሪ ስለማድረግ

1/ በዚህ መመሪያ መሰረት ተመልምለው ለሚመረጡ አማካሪዎች ከዚህ በታች ተዘርዝረው የተገለጹትን ሁኔታዎች የሚያሟላ የማስታወቂያ ጥሪ ይተላለፋል።

2/ የማስታወቂያ ጥሪው በተቻለ መጠን ለሁሉም ተደራሽ ይሆን ዘንድ ሰፊ ተደራሽነት ባላቸው መንግስታዊ የዜና ማሰራጫዎች በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥንና በጋዜጣ መተላለፍ ይኖርበታል።

## 6. ብቁ ያልሆኑ አማካሪ አሃዶች

ማንኛውም በአማካሪ አሃድነት ለመመዝገብ የቀረበ ማመልከቻ፣

1/ የአባላቱ የትምህርት ዝግጅት ወይም የሥራ ልምድ ማስረጃ በማታለል ተግባር ወይም በሐሰት የተገኘ መሆኑ ሲረጋገጥ፤

2/ በአባልነት ከቀረቡት የአሀዱ አባላት መካከል መስራት የማያስችለው የአካል ወይም የአእምሮ ጉድለት ያለበት መሆኑ ወይም ይህ መመሪያ የሚጠይቀውን መስፈርት የማያሟላ መሆኑ ሲረጋገጥ የአሀዱ የምዝገባ ማመልከቻ ተቀባይነት አይኖረውም።

## 7. የአማካሪ አሀድነት የምሥክር ወረቀት አሰጣጥ

1/ ከዚህ በላይ በአንቀጽ 3 ንዑስ ቁጥር /1/ ሥር የተመለከቱትን መሥፈርቶች ማሟላቱ የተረጋገጠ አማካሪ አሀድ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ሥር የተመለከተውን ደረጃ የአማካሪ አሀድነት የብቃት ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀት ይሰጠዋል ።

2/ በዚህ መመሪያ መሠረት ለአማካሪ አሀዱ የሚሰጠው የብቃት ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀት ምንም ዓይነት ገደብ አይጻፍበትም ።

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር /1/መሠረት የምሥክር ወረቀት የተሰጠው አማካሪ አሀድ በባለሙያዎች ማብቂያ መመሪያ መሠረት የተሰጠውን የምሥክር ወረቀት መመለስ ይኖርበታል።

## 8. የአሀዱ ህጋዊ ሰውነት

1/ አሀዱ ህጋዊ ሰውነት የሚኖረው አግባብ ባለው ህግ መሠረት ሲመዘገብ ነው።

2/ ከአሀዱ ህልውና ጋር በተያያዘ እያንዳንዱን የአሀድ አባል በሚመለከት ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር አሀዱ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚኖረው ግንኙነት አሀዱን የመወከል ሥልጣን ያለው በአሀዱ ማቋቋሚያ ሰነዶች የተመለከተው ሰው ወይም በእርሱ የሚወከለው ባለሞያ ይሆናል።

## 9. የአማካሪ አሀዶች የፕሮጀክት መጠን

አማካሪ አሀዶች ሊይዙት የሚችሉት የአንድ ፕሮጀክት መጠን በባለሙያዎች ማብቂያ መመሪያ ውስጥ ለሚካተቱ ፕሮጀክቶች በዚያው መመሪያ በተመለከተው መሠረት ሲሆን ከነዚህ ውጪ ባሉ ሌሎች ፕሮጀክቶች የሚሳተፉት በአጠቃላይ መመሪያው መሠረትና በዚህ መመሪያ መሠረት በተሰጣቸው ደረጃ ይሆናል፡፡

## 10. የምሥክር ወረቀትን ስለመሠረዝ

ማንኛውም በዚህ መመሪያ መሠረት ለአማካሪ አሀድ የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀት፣

1) የአባላቱ የትምህርት ዝግጅት ወይም የሥራ ልምድ ማስረጃ በማታለል ተግባር ወይም በሐሰት የተገኘ መሆኑ ሲረጋገጥ፤
2) በማናቸውም ምክንያት ለሌሎች መጠቀሚያነት ተላልፎ መሰጠቱ ሲረጋገጥ ፤
3) በሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ባለው ሌላ ህግ የአማካሪ አሃዱ ፈቃድ እንዲሠረዝ ሲወሰን፣ በመዝጋቢው አካል ሊሰረዝ ይችላል፡፡

## 11. የምስክር ወረቀትን ስለማገድ

1/ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 7 መሠረት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው አማካሪ አሀድ የምስክር ወረቀቱን ካገኘ በኋላ ከሥራ አፈጻጸም ጋር የተገናኘ ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋት ስለመፈፀሙ በጽሑፍ ጥቆማ ወይም አቤቱታ ሲቀርብበት መዝጋቢው አካል አሀዱ የተከሰሰበትን ጥፋት ስለመፈፀሙ እስኪጣራ ድረስ የተሰጠውን የምስክር ወረቀት ከአንድ ወር ላልበለጠ ጊዜ ሊያግደው ይችላል፡፡

2/ ሆኖም መዝጋቢው አካል የምሥክር ወረቀቱ እንዲታገድ በተደረገ አሀድ ወይም የአሀድ አባል ላይ በመዝጋቢው አካል ወይም በሌላ አመልካች በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

3/ መዝጋቢው አካል በዚህ የጊዜ ገደብ ውስጥ ስለዕገዳው መነሳት ወይም ሌላ ውሳኔ የሚሰጥ ከሆነ ይህንኑ ውሳኔ ለባለጉዳዩ በጽሁፍ መስጠት ወይም በመሥሪያ ቤቱ በግልፅ ቦታ ላይ መለጠፍ አለበት።

4/ በዕገዳው ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ያልተሰጠ እንደሆነ ይህ ጊዜ ሲጠናቀቅ በማንኛውም የአሀዱ አባል በሚቀርብ ማመልከቻ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው ዕግዱ ወዲያውኑ እንዲነሳ ይወስናል።

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር /1/ መሠረት ዕግድ የተሰጠበት አሀድ የዲሲፕሊን ጉዳይ በፌዴራል የግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የሚታይ ሆኖ ሲገኝ መዝጋቢው አካል በዚሁ የዕገዳ ጊዜ ውስጥ ጉዳዩን ለኤጀንሲው መምራት አለበት ።

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር /1/ መሠረት በሚሰጥ ዕገዳ ላይ ለቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አቤቱታ አይቀርብበትም።

7/ የአማካሪ አሀዱ ወይም አባላቱ ፈቃድ በአንቀጽ 10 ንዑስ ቁጥር /1/ መሠረት እንዲሠረዝ ሲወሰን ጥፋተኛው በሕግ እንዲጠየቅ ጉዳዩ ለሚመለከተው አካል መተላለፍ አለበት።

## ክፍል ሶስት
## የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት

### 12. አቤቱታ ስለማቅረብ

1/ በዚህ መመሪያ የሚሰጠውን የአማካሪ አሀድነት የብቃት ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀት ያልተሰጠው ወይም የተሰጠው የምሥክር ወረቀት በዲሲፕሊን ወይም በሌላ ምክንያት እንዲሠረዝ በመዝጋቢው አካል የተወሰነበት ወይም በአንቀጽ 11/2/ በተመለከተው ሁኔታ ዕገዳው ያልተነሳለት አሀድ መዝጋቢው አካል በሠጠው ውሳኔ ላይ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13 መሠረት ለሚቋቋመው ኮሚቴ ውሳኔው ወይም ዕገዳው አግባብ ያልሆነበትን ምክንያት አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል።

2/ አመልካቹ አሀድ ለኮሚቴው ቅሬታውን ማቅረብ የሚችለው በዚህ መመሪያ መሠረት የብቃት ማረጋገጫ የማይሰጠው መሆኑ ከተገለፀ ወይም ከመዝገብ

እንዲሠረዝ በመዝጋቢው አካል ውሳኔ በተሰጠ ወይም ውሳኔው በማስታወቂያ ከተገለፀ በ10 ቀናት ውስጥ ማቅረብ አለበት፡፡

3/ ሆኖም በአንቀጽ 11 /2/ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ዕገዳ ያልተነሳለት ወይም ጉዳዩ ውሳኔ ያልተሰጠው ወይም ለኤጀንሲው ያልተላከ አሀድ በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር /2/ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ሳይገታ በማንኛውም ጊዜ ጥያቄውን ለቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው ሊያቀርብ ይችላል፡፡

## 13. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ

1/ በዚህ መመሪያ መሠረት የሚቋቋመው የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ

ሀ) የከተማ ፕላን ቢሮ ተወካይ ................................ ሰብሳቢ

ለ) የኮንስትራክሽን ኢንደስትሪ ልማት ቢሮ ተወካይ ...... አባል

ሐ) የሕግ አገልግሎት መምሪያ ተወካይ .................. አባል

የሚገኙበት ይሆናል፡፡

2/ የኮሚቴው አብላጫ ድምጽ የሚሰጠው ውሳኔ የኮሚቴው ውሳኔ ይሆናል፡፡ ድምፅ እኩል ለእኩል ሲሆን በሰብሳቢው ድጋፍ ያገኘው ሀሳብ የኮሚቴው ውሳኔ ይሆናል፡፡

3/ አግባብ ያለው የሥራ ሂደት ለኮሚቴው በፀሀፊነት የሚያገለግል ሠራተኛ ይመድባል፡፡

## 14. የኮሚቴው የሥልጣን ወሰንና የውሳኔ አሰጣጥ

ኮሚቴው

1/ አንድ የአማካሪ አሀድ በማናቸውም ምክንያቶች ባለመመረጡ ወይም የአመልካቹን ማስረጃዎች ባለመቀበል አመልካቹ የምሥክር ወረቀት እንዳይሰጠው መዝጋቢው አካል በሚሰጠው ውሳኔ ላይ፣ እንዲሁም በአንቀጽ 11 /2/ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ውሳኔ ያልተሰጠበት የዕገዳ ትዕዛዝ እንዲነሳ የሚቀርበውን ቅሬታ ተቀብሎ የመጨረሻ ውሳኔ የመስጠት፣

2/ አመልካቹ አሀድ በሥራው ሂደት ወቅት በሚፈጽመው የዲሲፕሊን ጉድለት ከምዝገባ እንዲሠረዝ በመዝጋቢው አካል ሲወሰን የሚቀርበውን ቅሬታ

ተቀብሎ የተሰጠው ውሳኔ እንዲነሳ፣ እንዲፀና ወይም እንደገና እንዲታይ ለሚኒስትሩ የውሳኔ ሀሳብ የማቅረብ፣ ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

3/ ኮሚቴው የቀረበለትን ጨሳኔ መርምሮ የውሳኔ ሀሳብ ለማቅረብ የሚረዱ ማናቸውም ሰነዶችና ማስረጃዎችን በመስሪያ ቤቱ በኩል ማስቀረብና ማየት ይችላል፡፡

4/ ሚኒስትሩ የአመልካቹ ፈቃድ እንዲሰረዝ በኮሚቴው የቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ የሚቀበለው ሲሆን የአመልካቹ ፈቃድ እንዲሠረዝ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል ፡፡

## 15. ወቅታዊ መረጃ ስለመስጠት

መዝጋቢው አካል በማንኛውም ጊዜ በአማካሪ አሀዱ ላይ የተወሰዱ እርምጃዎችንና የተሰጡ ውሳኔዎችን እየተከታተለ ለሚመለከታቸው አካላት ወቅታዊ መረጃ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

## 16. ጥብቅ ክልከላ

1/ ማንኛውም በዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች መሠረት የብቃት ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀቱ የታገደበት ወይም የተሠረዘበት አማካሪ አሀድ የምሥክር ወረቀቱ ታግዶ ባለበት ወይም ተሠርዞ ባለበት ጊዜ ውስጥ ከመዝጋቢው አካል በልዩ ሁኔታ ለተወሰነ ጊዜ የሚቆይ ፈቃድ ካልተሰጠው በስተቀር በዚህ መመሪያ መሠረት የተፈቀዱ ሥራዎችን ሊያከናውን አይችልም፡፡

2/ መዝጋቢው አካል የምሥክር ወረቀቱ የተሠረዘበት ወይም የታገደበት አማካሪ አሀድ የምሥክር ወረቀቱ ተሠርዞ ወይም ታግዶ ባለበት ወቅት በዚህ መመሪያ መሠረት በተሰጠው የብቃት ማረጋገጫ ተመርኩዞ ባወጣው የንግድ ፈቃድ ሲንቀሳቀስ በሚገኝ ሥራ ተቋራጭ ላይ ሕጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ አግባብ ላለው አካል ማስተላለፍ አለበት፡፡

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 17. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ከዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ አግባብነት ያላቸው የባለሙያዎች የማብቂያ መመሪያ ድንጋጌዎች በዚህ መመሪያ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ፤ እንዲሁም ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም በማሟያነት ተፈጻሚ ይሆናሉ።

### 18. የማስፈፀም ኃላፊነት

የሚኒስቴሩ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ይህን መመሪያ የማስፈፀም ኃላፊነት ተሰጥቶታል ።

### 19. መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም ጊዜ ሊሻሻል ይችላል።

### 20. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከታህሣሥ 27 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ ይውላል።

**አዲስ አበባ ታህሣሥ 27 ቀን 2003 ዓ.ም**

**መኩሪያ ኃይሌ**

**የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስትር**